| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "በሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፡ ሀገር ፡ በስይጣኔ ፡ አይፈርስም!" |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2017-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## ኢትዮጵያ ፥ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ዋልታ ፡ እና ፡ ማገር ።



*"ዘፍ. ፥ 2 ፥ 13 ፤ የኹለተኛውም ፡ ወንዝ ፡ ስም ፡ ግዮን ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ይከባል ። "*

የመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ እና ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ አካባቢ ፡ የሦስት ፡ የብሶች ፡ መገናኛ ፡ እና ፡ የዓለም ፡ አንድ ፡ አራተኛ ፡ የንግድ ፡ ልውውጥ ፡ የሚተላለፍበት ፡ ዐቅዳዊ ፡ በር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በታሪክ ፡ ዐያሌ ፡ ጦርነቶችን ፡ ቀስቅሷል ፤ ዛሬም ፡ ቢኾን ፥ ኀያላኑ ፡ የጦር ፡ ሰፈሮቻቸውን ፡ አጠናክረው ፡ ገንብተውበት ፡ ተፋጥጠው ፡ ይገኙበታል ።

የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፥ ሲጠብ ፥ ኢትዮጵያን ፣ ሶማልያን ፡ እና ፡ ጂቡቲን ፡ አጠቃሎ ፥ 2 ፡ ሚልዮን ፡ ኪሎሜትር ፡ ማእዝን ፡ (ኪሜ$^2$) ፡ የወለል ፡ ስፋት ፡ እና ፡ 140 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች ፡ አሉት ።

ሲሰፋ ፡ ደግሞ ፥ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሱዳንን ፣ ደቡብ ፡ ሱዳንን ፣ ኬንያን ፣ ኡጋንዳን ፣ ሩዋንዳን ፣ ቡሩንዲን ፡ እና ፡ ታንዛንያን ፡ ይጨምራል ። የወለል ፡ ስፋቱም ፡ በ 2 ፡ ዕጥፍ ፡ ሰፍቶ ፡ 4 ፡ ሚልዮን ፡ ኪሜ$^2$ ፡ ሲደርስ ፥ የነዋሪዎቹ ፡ ብዛት ፡ ደግሞ ፡ 330 ፡ ሚልዮንን ፡ ያልፋል ። ከግብጽ ፡ እና ፡ ከኮንጎ ፡ በቀር ፥ የአባይ ፡ ተፋሰስ ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፡ ይገኙበታል ።

በጠባቡም ፡ ኾነ ፡ በሰፊው ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ቀጣና ፥ በሕዝብ ፡ ብዛትም ፡ ኾነ ፡ በመልክአ-ምድራዊ ፡ አቀማመጥ ፥ በጥንታዊ ፡ ሥልጣኔነትም ፡ ኾነ ፡ በሐራ ፡ ሀገርነት ፡ ታሪክ ፥ በባህላዊም ፡ ኾነ ፡ በጥርየታዊ ፡ ሀብት ፥ በመባሕታዊ ፡ ተሰሚነትም ፡ ኾነ ፡ በወታደራዊ ፡ ችሎት ፥ ኢትዮጵያ ፡ አንድያዋ ፡ የቀጣናው ፡ ኀያል ፡ ሀገር ፡ ናት ። ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፥ የቀጣናው ፡ ሀገሮችም ፡ ኾኑ ፡ የሩቅ ፡ መንግሥታት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያላቸው ፡ ከበሬታ ፥ ምንም ፡ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ እጅጉን ፡ ቢሸረሸርም ፥ እስካኹን ፡ ተወዳዳሪ ፡ አይገኝለትም ።

ያፍሪቃ ፡ የብስ ፡ በጠቅላላው ፡ የመዋሐድን ፡ ኺደት ፡ ዠምሯል ። በአፍሪቃ ፡ ደረጃ ፥ ቀረጥ-አልቦ ፡ ንግድ ፣ ይለፍ-አልቦ ፡ የሰዎች ፡ ዝውውር ፡ እና ፡ የመሳሰሉ ፡ የነጻ ፡ ገበያ ፡ ስምምነቶች ፡ ቀጣናዊም ፡ ኾነ ፡ የብሳዊ ፡ መዋሐዱን ፡ እያፋጠኑት ፡ ይኼዳሉ ።

በዚህ ፡ መኻከል ፥ ኢትዮጵያ ፡ የምትገኝበት ፡ ውንብድናዊ ፡ የአገዛዝ ፡ ኹኔታዋ ፥ ያሏትን ፡ ብልጫዎች ፡ ኹሉ ፡ ዐጥታ ፥ ከግንባር-ቀደምነት ፡ ይልቅ ፡ በተርታ ፡ ጭፍራነት ፡ የምትመራበት ፡ አደጋ ፡ አመዝኗል ። የአፍሪቃ ፡ የብስ ፡ የመዋሐድ ፡ ኺደት ፡ ተፋጥኗል ። ኢትዮጵያም ፡ ፈጥና ፡ ግዛታዊ ፡ የውስጥ ፡ ችግሯን ፡ በመፍታት ፥ ሙሉ ፡ ችሎታዋን ፡ በመገንዘብም ፥ በዐጪር ፡ ጊዜ ፡ የአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ቀጣናዊ ፡ ምስትግባሯን ፡ ማስለጥ ፡ ትችላለች ❖

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።